## ምድብ አንድ (የሙዓለ ሕፃናት ተማሪዎች)

## 35 ኛ ሳምንት

# መልአኩ ቅዱስ ጴጥሮስን ከእስር አስፈታው

**ዓላማ፡-**

- የጸሎትን ኃይልና የቅዱሳን መላእክትን ተራዳኢነት በቅዱስ ጴጥሮስ እስር ላይ ተመርኩዘን መማር።

**ምንባብ፡-**

- የሐዋ.ሥራ 12÷1-19

**መግቢያ**

- ቅዱስ ጴጥሮስ ማን እንደሆነ ታስታውሳላችሁ? አዎን ከ12ቱ ሐዋርያት አንዱ ነው።
- በዛሬው ትምህርታችን በእግዚአብሔር መልአክ እርዳታ ከእስር ቤት መፈታቱን እንማራለን።

**ትምህርቱ**

- ሄሮድስ የተባለ ጨካኝ ንጉስ ነበር። የክርስቶስ ወዳጅ የነበሩትንና ደቀመዛሙርቱን በኢየሱስ ክርስቶስ እንዳያምኑና እንዳያስተምሩ ያንገላታቸው ነበር።
- አንድ ቀንም ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማስተማሩ ቅዱስ ጴጥሮስን አሰረው።ሐዋርያው ግን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደነበር አስተውሎ አልፈራም።በሌሊት ቅዱስ ጴጥሮስ በእስር ቤት ተኝቶ ሳለ የእግዚአብሔር መልአክ ተገለጠ ብርሃኑም አንጸባረቀ።
- መልአኩ ቅዱስ ጴጥሮስ ጎኑን መቶት ቀሰቀሰውና ጫማውንና ልብሱን አድርጎ እንዲከተለው አዘዘው።
- የቅዱስ ጴጥሮስ እጅና እግር በሰንሰለት ታስሮ ነበር፣መልአኩ ሲናገር ግን የእጅና እግሩ ሰንሰለት ተፈትቶ ወደቀ።
- ቅዱስ ጴጥሮስም መልአኩ እየመራው ከእስር ቤት ወጥቶ መንገድ ዳር ደረሰ።ከዚያም ቅዱስ ጴጥሮስ ወደ ቤቱ ሄደ።
- ቅዱስ ጴጥሮስ ቤቱ ሲደርስ በዚያ ተሰብስበው እንዲፈታ ሲጸልዩ የነበሩት ሁሉ ተደሠቱ።እግዚአብሔርንም አመሰገኑ።
- እግዚአብሔርም ጸሎታቸውን ሰምቶ መልአኩን ልኮ ቅዱስ ጴጥሮስን አዳነው።

**ልምምድ**

1. ቅዱስ ጴጥሮስ ከ12ቱ የጌታችን ------------------------- አንዱ ነው።
2. ቅዱስ ጴጥሮስን ያሠረው ንጉስ ማን ይባላል?
3. ቅዱስ ጴጥሮስ ከእስር የተፈታው እንዴት ነበር?

**መዝሙር**

ተናገሩ ድንቅ ሥራውን መስክሩ (2)

ተዓምሩን ለዓለም ንገሩ (2)

ድንቅ ስራውን መስክሩ

# Praised be God, Who helped Me



ይቆየን።